# ታውቁኛላችሁ?



6-9ኛው ሳምንት

2ኛ ክፍል

መጽሐፍ 3

# ታውቁኛላችሁ?

መጽሐፍ 3 | 2ኛ ክፍል | 6-9ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ::

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



ለማዳ እንስሳ ነኝ:: አራት እግሮችና ሁለት ጆሮዎች አሉኝ:: ዘወትር ሥጋ መመገብ እመርጣለሁ:: ሥጋ ባላገኝም ሰዎች የሚመገቡትን እመገባለሁ:: ሰዎች በታማኝነቴ ያሞግሱኛል::



ለሊትም ቀንም የአሳዳሪዎቼን
ቤት በትጋት እጠብቃለሁ፡፡
ኮሽ ባለ ቁጥር የቤቱን
ግቢ እየተዘዋወርኩ እቃኛለሁ፡፡
እንግዳ ነገር ከሌሎች
እንስሳት የበለጠ ከሩቅ
የማሽተት አቅም አለኝ፡፡



አሳዳሪዎቼ ምግብ ቢሰጡኝም
ባይሰጡኝም ከቤት አልርቅም::
በጣም ከራበኝ እጥፍጥፍ
ብዬ እተኛለሁ::

ከጠገብኩ ደግሞ ጅራቴን ከወዲያ ወዲህ እያወዛወዝኩ ከአሳዳሪዎቼ እግር ስር አልለይም።

ረሀብ ሲጠናብኝ አላዝናለሁ::
አንዳንድ ሰዎች ማላዘኔን
የመጥፎ ምሳሌ ያደርጉታል::
ሳላዝን ከሰሙ ዝም
ለማሰኘት ይመቱኛል::
ከአጠገባቸው ያባርሩኛል::

ማላዘኔን እንዳቆም ሰዎች ምግቤን በሰአቱ ሊሰጡኝ ይገባል። መኝታዬንም ማዘጋጀት አለባቸው። ንፅህናዬን ዘወትር መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

መኝታዬን መጥረግ ሰውነቴን ማጠብ፣ የምመገብበትን ዕቃ ማፅዳት፣ የምፀዳዳበትን ቦታ ማዘጋጀት አለባቸው።




በሃኪም ሊያስከትቡኝና ሊያስመረምሩኝ ይገባል።
ካልተመረመርኩና ካልተከተብኩ በሽታ ይይዘኛል።

መታመመሜን ሰዎች በቶሎ ላይረዱ ይችላሉ። በሽታው እየጠናብኝ ሲሄድ ያገኘሁትን ሰው ሁሉ እነክሳለሁ። በሽታው ከእኔ ወደሰዎች በቀላሉ ይተላለፋል። በሽታው ወደሰዎች ከተላለፈ ለሞት ይዳርጋቸዋል። አሁን አወቃችሁኝ?

USAID
ከአሜሪካን ህዝብ